መልእክት አምስት

## የሕይወት ዛፍ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘፍ. 2፥7-9፤ ራእ. 2፥4-5፣ 7፤ 22፥2፣ 14፤
2 ቆሮ. 4፥5፤ 5፥14-15

I. **ክርስቶስ እንደ ሕይወት የአጽናፍ ዓለም ማዕከል የሆነው የሕይወት ዛፍ እውነታ ነው፤ ሕይወት የእግዚአብሔር ፍጥረት ግብ (ዘፍ. 1፥26-28፣ 31፤ 2፥7-9) እና የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን ግብ ነው (ዮሐ. 19፥34፤ ሮሜ 5፥10፤ ራእ. 22፥1-2፣ 14፣ 19)፡-**

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ዛፍ ሁልጊዜ የሚያመለክተው ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ብልጥግናዎች ሁሉ አካል መልበስ ለምግባችን መሆኑን ነው፤ እግዚአብሔር ሰውን በሕይወት ዛፍ ፊት ማስቀመጡ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሰው ቅንብር ይሆን ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን በሕይወታዊ መንገድ በመብላት እና በገንባፍራሽ ቅንባሮ በማብላላት እንደ የሰው ሕይወት እንዲቀበለው እንደፈለገ ነው—ቆላ. 2፥9፤ ዘፍ 2፥9፤ ዮሐ. 1፥4፤ 10፥10፤ 14፥6፤ 15፥1፤ 6፥35፣ 57፣ 63፤ 1 ቆሮ. 15፥45።

ለ. በራእይ 2፥7 ያለው የሕይወት ዛፍ፣ የተሰቀለውና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ በእግዚአብሔር ለተዋጁት ሕዝቡ ሁሉ ለዘላለም ምግብ ለመሆን የሕይወት ዛፍ በሚሆንባት መጠናቀቂ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በሆነችው (ራእ. 22፡2፣ 14) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬ ያለውን የተሰቀለውን (እንደ እንጨት በዛፉ የተመለከተውን—1 ጴጥ. 2፥24) እና ከሞት የተነሣውን (በእግዚአብሔር ሕይወት የተመለከተውን—ዮሐ. 11፥25) ክርስቶስ ያመለክታል።

II. **የእግዚአብሔር ሕይወት በሰው ውስጥ የሚያጋጥሙትን እንቅፋቶች ማየት ያስፈልገናል፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር ሕይወት በውስጣችን የሚያጋጥመው የመጀመሪያው ችግር የሰዋዊ ፅንሰ-ሃሳቦቻችንን ጨለማነት አለመገንዘባችን ነው፡-

1. በክርስትና ሕይወት ውስጥ ብቸኛው አስፈላጊ ነገር በውስጣችን ላለው ሕያዉ ክርስቶስ እንዴት ግድ እንደምንሰኝ መሆኑን ማየት ያስፈልገናል—ገላ. 1፥16፤ 2፥20፤ 4፥19፤ ፊልጵ. 1፥19-21፤ ኤፌ. 4፥13፤ 2 ቆሮ. 3፥18።
2. ክርስቲያን መሆን ማለት ከክርስቶስ ውጪ ማንኛውንም ነገር ግባችን አድርገን አለመውሰድ ማለት ነው፤ ብዙ ሰዎች ከዳኑ በኋላ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ችግር የሚገጥማቸው የሕይወትን መንገድ ስለማያውቁ እና ክርስቶስን እንደ ሕይወታቸው ስለማይወስዱ ነው።

ለ. ሕይወት በውስጣችን የሚያጋጥመው ሁለተኛው ችግር ግብዝነት ነው—ማቴ. 6፥2፣ 5፤ 7፥5፤ 23፥13-29፡-

1. የአንድ ሰው መንፈሳዊነት የሚወሰነው በውጫዊ ገጽታ ሳይሆን በውስጡ ለሚኖረው ክርስቶስ ግድ በመሰኘቱ ላይ ነው።
2. ተፈጥሯዊ መልካምነታችን የውሸት መንፈሳዊነት ነው፣ እንዲያውም ለሕይወት ትልቅ እንቅፋት ነው፤ የሕይወት መገለጥ ተፈጥሯዊ ጸባያችንን እና ምርጫችንን መግፋትን እና ክርስቶስ በእኛ እንዲሠራ እና እንዲሰብረን መፍቀድን ብቻ ያካትታል።
3. ነገሮችን ሁልጊዜ በጸባያችን እና በተፈጥሯዊ ማንነታችን መሠረት የምናደርግ ከሆነ፣ ውጤቱ ሁሌም ግብዝነት ይሆናል።

ሐ. ሕይወት በውስጣችን የሚያጋጥመው ሦስተኛው ችግር ዓመፅ ነው፡-

1. ክርስቶስ ስለ ፈቃዱ እና ከእኛ ስለ ሚጠይቃቸው ነገሮች፣ ስለ ምሪቱ እና እኛን ስለ ማደቡ ግልጽ ሊያደርግልን በውስጣችን ይሠራል፣ ይንቀሳቀስማል።
2. ሆኖም፣ ምሪቱን ባለመቀበል ወይም ዋጋ ባለመክፈል ሳንታዘዝ በውስጣችን ካለው ስሜት በተጻራሪ ከሄድን፣ ይህ አለመፍቀድ እና ተቃውሞ ዓመፅ ነው።
3. በጣም በተደጋጋሚ እና በጣም ከባድ የሆነው የምንሠራው ኃጢአት ውጫዊ እና የሚታይ አይደለም፤ በምትኩ፣ በውስጣችን ያለውን የክርስቶስን ስሜት ያለመታዘዝ ኃጢአት ነው፤ ክርስቶስ በውስጣችን እየኖረ ነው፣ ያለማቋረጥም ውስጣዊ የሕይወት ስሜትን እየሰጠን ነው—ሮሜ 8፥6፤ 1 ዮሐ. 2፥27።

መ. ሕይወት በውስጣችን የሚያጋጥመው አራተኛው ችግር ተፈጥሮአዊ ብቃታችን ነው፡-

1. ብዙ ወንድሞችና እኅቶች ጌታን የእውነት ይወዱታል፣ ለጌታም ቀናተኞች ናቸው፣ በጣም እግዚአብሔርን የሚፈሩም ናቸው፤ ይሁን እንጂ፣ ትልቁ ችግራቸው የብቃቶቻቸውና የችሎታዎቻቸው ጥንካሬ እና ታላቅነት ነው፤ ከዚህ የተነሣ፣ ክርስቶስ በውስጣቸው ስፍራ ወይም መንገድ የለውም።

2. ብቁ እና ተሰጥዖ ያለን ልንሆን እንችላለን፣ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች እንደ ኃጢአት ወይም ርኩሰት አንቆጥራቸውም፤ ተፈጥሮአዊ ብቃቶቻችንን በመናቅ ምትክ እንደ ውድ ነገር እንመለከታቸዋለን፤ በውስጣችን ሳይሰበሩ ከቀሩ፣ ለክርስቶስ ሕይወት ችግር ይሆናሉ።

ሠ. በውስጣችን ላሉት ለእነዚህ እንቅፋቶች ሁሉ አንድ መፍትሄ አለ—የግድ በመስቀሉ ማለፍ እና መስቀሉ እንዲሰብረን መፍቀድ አለብን፤ የክርስቶስ ሕይወት በውስጣችን እንዳይከለከል ከፈለግን፣ የመስቀሉን መስበር መለማመድ እና እነዚህ እንቅፋቶች በማደብ ውስጥ እንዲያልፉ እና እንዲወገዱ መፍቀድ አለብን—ማቴ. 16፥24-25።

III. **ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ እንበላው ዘንድ፣ በነገር ሁሉ የመጀመሪያውን ስፍራ ልንሰጠው ይገባል፣ ይህም እርሱን በሕይወታችን ውስጥ እንደ ሁሉ ነገር እንድንቆጥረውና እንድንወስደው በፍቅሩ ግድ በመሰኘት እርሱን በመጀመሪያው ፍቅር መውደድ ነው—ራእ. 2፥4-5፤ ቆላ. 1፥18፤ 2 ቆሮ. 5፥14-15፤ ማር. 12፥30፤ መዝ. 73፥25-26፤ 80፥17-19፡-**

ሀ. ጌታን በመጀመሪያው ፍቅር መውደድ፣ በነገር ሁሉ የመጀመሪያውን ስፍራ ለእርሱ መስጠት፣ እርሱን እንደ ሕይወት ዛፍ መብላት ነው፤ ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ መብላት፣ ማለትም፣ ክርስቶስን እንደ የሕይወት አቅርቦታችን መደሰት፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ቀዳሚው ጉዳይ ሊሆን ይገባል—ራእ. 2፥7፤ ዮሐ 6፥57፣ 63።

ለ. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይዘት ክርስቶስን በመደሰታችን ላይ ይመረኮዛል፤ ይበልጥ እሱን በተደሰትን መጠን፣ ይዘቱ ይበልጥ የበለጠገ ይሆናል፤ ነገር ግን ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ መብላት፣ እርሱን እንደ የሕይወት አቅርቦታችን መደሰት፣ እርሱን በመጀመሪያው ፍቅር መውደዳችንን ይጠይቃል— ራእ. 2፡4-5።

ሐ. በአንድ በኩል፣ በትክክል ለመናገር፣ በራእይ 2፡7 ላይ ያለው በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ካለው ከሕይወት ዛፍ መብላት፣ በሚመጣው የሺህ ዓመት መንግሥት በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ እንደ የሕይወት አቅርቦታችን ክርስቶስን ልዩ በሆነ መንገድ መደሰትን ያመለክታል።

መ. በሌላ በኩል፣ የተሰቀለውንና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ እንደ የሕይወት ዛፍ፣ በመንፈሳችን ውስጥ እንዳለ የምግብ አቅርቦት፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንደ ቅድመ ቅምሻ እየተደሰትነው ነው፤ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንደሰተው ዘንድ ክርስቶስ የሕይወት ዛፍ የሆነበት የእግዚአብሔር ገነት ነው።

ሠ. በነገር ሁሉ ለጌታ የመጀመሪያውን ስፍራ ስንሰጥ እና የተሰቀለውን እና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ ቀኑን ሙሉ እንደ የሕይወት ዛፍ መብላታችንን ስንጠብቅ፣ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታዋ ምንም ይሁን ምን ገነት ትሆንልናለች፤ ስለዚህም፣ ለቤተ ክርስቲያን ያለን ስሜት እና አመለካከት በሁኔታችን ላይ የሚመረኮዝ ነው።

ረ. “ክርስቶስን በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንደ የሕይወት ዛፍ ዛሬ ካልተደሰትን፣ በእርግጠኝነት በመንግሥቱ ዘመን በሕይወት ዛፍ ውስጥ አንሳተፍም። በልምምዱ መሠረት ዛሬ በአናሄይም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ለእኔ ገነት ናት”—*The Collected Works of Witness Lee*, 1994–1997, vol. 5, “The Vital Groups,” p. 157።

ሰ. ለቤተ ክርስቲያን ባድማነት እና መዝቀጥ ውስጠ-መሠረታዊው ምክንያት ክርስቶስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ከፍ ከፍ አለመደረጉ ነው፤ በነገር ሁሉ ፊተኛውን ስፍራ፣ የመጀመሪያውን ስፍራ አይሰጡትም፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእያንዳንዱ የኑሯቸው ገጽታ ፊተኛውን ስፍራ በመስጠት ክርስቶስን ከፍ ከፍ ባደረጉት ጊዜ ሁሉ፣ መታደስ እና መነቃቃት አለ— መዝ. 80፥17-19።

ሸ. ክርስቶስ በሕይወታችን ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመልእክቶቻችንም ሁሉ ውስጥ የመጀመሪያው ስፍራ ሊኖረው ይገባል፤ “ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፥ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን”—2 ቆሮ. 4፥5፤ ተዛ. ዕብ. 1፥3፤ 8፥1፤ 12፥2፤ መዝ. 80፥1፣ 17-19፤ 110፥1-7፡-

1. በሥራችን ሰዎችን ያለማቋረጥ ወደ ማዕከሉ መሳብ እና “ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ” እንዲያዩ ማድረግ አለብን፤ ለጌታ ኢየሱስ በዙፋኑ ላይ ስፍራውን መስጠት አለብን—ተዛ. መኃ. 1፥1-4፤ ኢሳ. 6፥1፣ 3፤ ዮሐ. 12፥41።
2. እንዲህ ያለውን መልእክት ለመስጠት፣ እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር መሰበር እና ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ እንዲኖረው መፍቀድ አለብን፤ መልእክታችን ማንነታችን ብቻ ነው—2 ቆሮ. 4፥10-13፤ ዮሐ. 12፥24-26፤ ተዛ. ሉቃ 12፥49-50።
3. የጌታ “መልካም አደረግህ” የሚለው ንግግር ከዓለም ምስጋናዎች ሁሉ ይበልጣል፤ የሰማይ ፊት ፈገግታ ከምድር የቁጣ ፊቶች ሁሉ ይበልጣል፤ የሰማይ ማጽናናት ከምድር እንባዎች ሁሉ ይበልጣል—ማቴ. 25፥21፣ 23፤ ኤር. 1፥7-9፣ 18-19፤ ዳን. 4፥26።

ቀ. በነገር ሁሉ ለክርስቶስ የመጀመሪያውን ስፍራ ለመስጠት፣ እንደ ንጉሣችን ለእርሱ በስሜት የተሞላ ፍቅር ሊኖረን ይገባል፤ ያኔ አንደበታችን እርሱ በሆነው ሁሉ መሠረት እርሱን በመለማመዳችን እና በመደሰታችን

ለእርሱ ያለንን ፍቅር እና ውዳሴ ለመጻፍ እንደተዘጋጀ እንደ ፈጣን ጸሐፊ ብዕር ይሆናል፣—መዝ. 45፥1-2፤ 2 ቆሮ. 3፥3፣ 6።

በ. ጌታን በመጀመሪያው ፍቅር መውደድ፣ በነገር ሁሉ ለእርሱ የመጀመሪያውን ስፍራ መስጠት ማለት እርሱን ማዕከላችን—የሚይዝ ማዕከላችን—እና አጽናፍ ዓለማችን—ሁሉ ነገራችን—አድርጎ መውሰድ ነው፤ እርሱን የግል አጽናፍ ዓለማችን ማዕከል፣ ይዘት እና የክበብ ዳርቻ አድርገን ልንወስደው ያስፈልገናል—ቆላ. 1፥17፣ 18።

ተ. ጌታን በመጀመሪያው ፍቅር መውደድ፣ በነገር ሁሉ ለእርሱ የመጀመሪያውን ስፍራ መስጠት ማለት ውበቱን አተኩሮ ማየት እና በእያንዳንዱ የክርስትና ሕይወታችን እና ሥራችን ዝርዝር ውስጥ የያሕዌን ምክር መጠየቅ ነው—መዝ. 27፥4፤ ኢ.ያ. 9፥14፤ ፊልጵ. 4፥6-7።

ቸ. ጌታን በመጀመሪያ ፍቅር መውደድ፣ በነገር ሁሉ ለእርሱ የመጀመሪውን ስፍራ መስጠት ማለት ምርኮኞቹ በመሆን እና "ጌታ ሆይ፣ አሸንፈኝ። የአንተ ምርኮኛ አድርገኝ። ፈጽሞ እንዳሸንፍ አትፍቀድልኝ። ሁልጊዜ አሸንፈኝ" ብሎ በመጸለይ በመንፈሳችን ውስጥ ላለው ዕረፍት ግድ በመሰኘት በተዋሐደው መንፈሳችን ቁጥጥር ሥር መሆን፣ መገዛት፣ አቅጣጫ መያዝ፣ መመራት እና መንቀሳቀስ ነው—2 ቆሮ. 2፥13-14።

ኀ. ጌታን በመጀመሪያ ፍቅር መውደድ፣ በነገር ሁሉ ለእርሱ የመጀመሪያውን ስፍራ መስጠት ማለት በላዩ የእግዚአብሔር የሰንፔር ዙፋን እንዳለበት እንደሚያስፈራ ብርጭቆ የጠራ ሰማይ ያለን መሆን ነው፤ ይህ ማለት በእኛ እና በጌታ መካከል ምንም ነገር የለም፣ እኛም እርሱን እንደ ንጉሣችን በመውሰድ እና በውስጣችን እንዲገዛ እና እንዲነግሥ በመፍቀድ በሚገዛ መገኘቱ ሰማያዊ ድባብ፣ ውስጣዊ ሁኔታ እና ውጫዊ ሁኔታ ተሞልተናል ማለት ነው—ሕዝ. 1፥22፣ 26።

ነ. የዛሬውን ዓለም ችግሮች መፍታት የሚችለው ንጉሡ ክርስቶስ በንግሥናው ከሚረዱት ከድል ነሺዎቹ ጋር በምድር ላይ ሲነግሥ ብቻ ነው (ኢሳ. 42፥1-4)፤ የክርስቶስ ስም በትውልዶች ሁሉ ይታወሳል፣ በድል ነሺዎቹ እና አብረውት በሚነግሡት ቅዱሳን በኩልም በአሕዛብ ይወደሳል (መዝ. 45፥16-17፤ ራእ. 2፥26)።

ኘ. በጽዮን የተመሰሉት ድል ነሺዎቹ ጌታ ምድርን ሁሉ የራሱ ሊያደርግ የሚመለስበት መነሻ ነጥብ ናቸው—መዝ. 48፥2፤ ዳን. 2፥34-35።

አ. "እናንተ ደጆች ቀና በሉ፣ ቀና በሉ፤ እናንተ የዘላለም በሮች፣ የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ! ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? [ያሕዌ] ነው ብርቱና ኃያል፤ [ያሕዌ] ነው በውጊያ ኃያል።...ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? የሠራዊት [ያሕዌ] ፣ እርሱ የክብር ንጉሥ ነው"—መዝ. 24፥7-8፣ 10 (አ.መ.ት.)፦

1. በሮቹ የአሕዛብ ከተሞች ናቸው፤ ደጆቹ የሰዎች ቤቶች ናቸው፣ ክርስቶስ ደግሞ የአሕዛብ ሁሉ መሻት ነው (ሐጌ 2፥7)፤ አሕዛብ ሁሉ፣ በጥቅሉ፣ ክርስቶስ እንዲመጣ እየተጠባበቁ ናቸው፣ ነገር ግን ክርስቶስ በሰዋዊ ፅንሰ-ሃሳባችን መሠረት ቶሎ አይመጣም (2 ጴጥ. 3፥8-9)፤ ስለዚህም፣ ራሳችንን ቀና ማድረግ እና መምጣቱን በትዕግሥት መጠበቅ እና መጠባበቅ ያስፈልገናል።
2. የክብር ንጉሥ፣ የሠራዊት (ማለትም፣ የጦር ሠራዊት) አምላክ፣ በአሸናፊውና ድል በሚነሣው ክርስቶስ አካል የለበሰው (ሉቃ. 21፡27፣ ማቴ. 25፡31) የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ነው፣ ያሕዌ ኢየሱስ ነው፣ ኢየሱስ ደግሞ በውጊያ ብርቱ እና አሸናፊ የሆነው ሥጋ የለበሰው፣ የተሰቀለው እና ከሞት የተነሣው ሦስታንዱ አምላክ ነው (1፥21፤ ራእ. 5፥5)።
3. እርሱ መላውን ምድር መንግሥቱ አድርጎ የራሱ ለማድረግ ከድል ነሺዎቹ ጋር በትንሣኤ ተመልሶ የሚመጣው ነው—ዳን. 2፥34-35፤ 7፥13-14፤ ኢዮኤል 3፥11፤ ራእ. 11፥15፤ 19፥13-14።

ከ. በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ እንዳለው ማንነት ክርስቶስ የሰርዲኖን (ቀይ ቀለሙ ቤዛነትን በማመልከት) እና የኢያስጲድ (ጥቁር አረንጓዴ ቀለሙ ሕይወትን በብልጥግናው በማመልከት) መልክ አለው፤ ስለዚህም፣ ራሳችንን ለክርስቶስ ራስነት ስናስገዛ እና በዙፋኑ ሥር ስንሆን፣ ከክብር አምላክ ጋር በበለጠገ ሕይወቱ አንድ ዓይነት መልክ ይኖረን ዘንድ በፍትሃዊ ቤዛነቱ እና በሕይወታዊ ማዳኑ ውስጥ እርሱ በሆናቸው ነገሮች ሁሉ ተጠቃሚዎች ነን—4፥3፤ 21፥10-11፤ ሮሜ 5፥10።

ኸ. በክርስቶስ የሚቤዥ ደም ልብሳቸውን የሚያጥቡ በቅድስቲቱ ከተማ፣ በእግዚአብሔር ገነት እንደ ዘላለማዊ እድል ፈንታቸው የሕይወትን ዛፍ ለዘላለም የመደሰት መብት አላቸው—ራእ. 22፥14፤ 2፥7።

© 2025 Living Stream Ministry